*DPR

oc QtrAiirMCHT or rAXKS AND HIXIUATION

* * * *
* *
WE APE
DC

# ስብሰባ ወይም ዝግጅት ለማካሄድ እያቀዱና ቤተሰቦችዎን፣ ጓደኞችዎን፣ ማህበርተኞችዎን ወይም የሥራ ባልደረባዎችዎን ለመጋበዝ ተስማሚ የሆነ ቦታ ያስፈልጎዎታል? የዲሲ የፓርክና የመዝናኛ መሥሪያ ቤትን ግሩም የሆኑ መገልገያ ቦታዎች፣ ፓርኮች፣ ሜዳና መዋኛዎችን ይመልከቱ።

## አድራሻችን


**DPR Permits Office**
1250 U St., NW, First Floor
Washington, DC 20009
ሜትሮ፣ አረንጓዴ/ቢጫ መስመር
U St/African-Amer Civil War Memorial/Cardozo Station

ስልክ፣ (202) 671-2597 Email: dprpermits@dc.gov
ድህረ ገጽ፣ dpr.dc.gov


የስራ ሰዓት: ሰኞ - አርብ • 9:00 am - 5:00 pm

### ፈቃድ ለማግኘት የት ማመልከት እችላለሁ?

ማመልከቻው በድህረ ገፃችን፡ DPR.DC.GOV ይገኛል። መገልገያ ቦታ እና ፈቃዶች፣ ፈቃዶች እና ቦታ መያዣ የሚለውን ይጫኑ።

### ፈቃድ የሚያስፈልገው መቼ ነው?

ማንኛውም ቡድን/ግለሰብ፣ የDPRን ፓርክ፣ መገልገያ ቦታ፣ ሜዳ ወይም መዋኛ ለመጠቀም ፈቃድ ያስፈልገዋል። መገልገያ ቦታዎች እና መዋኛዎቹ በተገለጸው መገልገያ ሰዓቶች ብቻ የተፈቀዱ ይሆናሉ። ፓርኮች በጨለማ ይዘጋሉ።

### ፈቃድ ለማግኘት ክፍያው ምን ያህል ነው?

ክፍያው እንደ ዝግጅቱ ዓይነትና እንደ ቦታ አያያዙ ይሆናል። አጠቃላይ የክፍያ ዝርዝር በድህረ ገጻችን ይገኛል።

### የተከፈለ እና የተሰጠኝን ፈቃድ መቼ መሰረዝ እችላለሁ?

ሁሉም ስረዛዎች ለፈቃድ ቢሮ በጽሁፍ (በኢሜል፣ በፋክስ ወይም በደብዳቤ) በቀጥታ መግባት አለባቸው። ስለ ተመላሽ ገንዘቦች ማብቂያዎች ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ።

ከዝግጅቱ ቀን 30 ቀናት በፊት ወይም ከዚያ በላይ የሚደረጉ ስረዛዎች፣ ቅድመ ክፍያውን ሙሉ በሙሉ እና ከፈቃድ ክፍያው 75% ተመላሽ ያገኛሉ። ከዝግጅቱ ቀን 30 ቀናት ያነሰ የሚደረጉ ስረዛዎች፣ ቅድመ ክፍያውን ብቻ ሲያገኙ፣ ከፈቃድ ክፍያ ምንም ተመላሽ አያገኙም።

### ለፈቃዱ እንዴት መክፈል እችላለሁ?

ሁሉም በፈቃድ ቢሮው በኩል የሚደረጉ ኪራዮች ፈቃዱ ከመሰጠቱ በፊት በሙሉ መከፈል አለባቸው። በኦንላይን፣ በክሬዲት ካርድ (ቪዛ፣ ማስተር ካርድ ወይም ዲስካቨሪ ብቻ)፣ በግንባር በመቅረብ፣ ክሬዲት ካርድ (ቪዛ፣ ማስተር ካርድ ወይም ዲስካቨሪ ብቻ) ለDC Treasurer ተብሎ የተፃፈ ቼክ ወይም መኒ ኦርደር። ጥሬ ገንዘብ አንቀበልም።

### የስፖርተኛ "የፈቃድ ክፍተት" ምንድን ነው?

DPR የኳስ ሜዳዎቹን እና የቅርጫት ኳስ መጫወቻ ስፍራውን ወቅታዊ ፈቃድ ይሰጣል። DPR ሁለት የተወሰኑ ወቅቶች አሉት፡ መጸው/ክረምት እና ፀደይ/በጋ። በአሁኑ ጊዜ ያለው ወቅታዊ የስፖርተኛ ፈቃድ መረጃ ዝርዝር በድህረ ገጻችን ይገኛል።

### የDPR ወቅታዊ የስፖርተኛ ፈቃድ ምርጫ ምንድን ነው?

ማመልከቻው በጊዜው እስተጠየቀ ድረስ፣ DPR፣ ሜዳዎቹን ለሚፈቀደው ወቅት በሚያዘጋጅበት ጊዜ፣ በሚከተለው የአማራጭ ቅደም ተከተል ሜዳውን ይሰጣል፡

1. DPR ፕሮግራሞች
2. DC የሕዝብ ትምህርት ቤቶች እና የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች
3. DPR ተባባሪዎች (ከDPR ጋር የህብረት ስምምነት የፈጸሙ ድርጅቶች)
4. የግል የወጣት ሊግ እና ቡድኖች
5. የግል የአዋቂዎች ሊግ

CAPRA

dpr.dc.gov